ዝንቱ ውእቱ ትእምርተ ሰላምነ

ዘረሰዮሙ እሐደ ለክልዔሆሙ ፡ ኤፌ ም ፪ ቍ ፲፬

፲፰ኛ ዓመት ቍጥር ፫

እ ፡ እ ፡ መስከረም ፳፱ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ. ም.

# ተክለ፡ሃይማኖት።

ይህ ድርስት ለሃይማኖትና ለምግባር ለጊዜውም ዜና መዋዕል መግለጫ የንባቡን ቀጥተኛ ትርጓሜ ከመከተል ጋር ስለ ታላቁ ኢትዮጵያዊ ሐዋርያ መታሰቢያ ተክለ ሃይማኖት ተብሎ ተሰየመ ።

የድርስቱ ዋጋ ባገር ውስጥ ባመት ብር 1.20
» » አንዱ 0.5
ለውጭ አገር እጥፍ ይሆናል ።

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የታሪክና ዜና ማደራጃ ጽሕፈት ቤት ኀላፊነት ታተመ ።

በወር ሁለት ጊዜ ይወጣል ።
የስልክ ቍጥር 130991
የፖስታ ሳጥን ቍጥር 1283

## ብዙኃን ማርያም ።

ብዙኃን ማርያም ማለት የብዙዎች እመቤት ማርያም ማለት ነው ። የብዙኃን ማርያም በዓል የሚከበርበትንና የስሙን ትርጓሜ ምክንያት በሚከተለው መሥመር በአጭሩ ለማስረዳት እንሞክራለን ።

በዚህ ዕለት ፩ኛ ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ፫፻፳፭ ዓ. ም. ቈስጠንጢኖስ በነገሠ በ፲፱ኛው ዓመት አርዮስ « ወልድ ፍጡር ነው» ብሎ ስለ ክደ እሱን ተከራክሮ ለማሳመን ፤ እምቢ ቢል ከማኅበረ ምእመናን ለመለየት 2340 ኤጲስ ቆጶሳት በንጉሡ በቈስጠንጢኖስ አዋጅ መሠረት ከሚያዝያ (ከግንቦትም የሚሉ አሉ) ፳፩ ቀን ጀምረው እስከ መስከረም ፳፩ ቀን በኒቅያ ላይ ተሰበሰቡ ፤ ክርክሩንም ቀጠሉ ።

ጉባኤውም ኅዳር ፱ ቀን ከፍጻሜ ደርሶ አርዮስ ተረታ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንም ኃይል ተገለጠ ።

ከ2340 ሊቃውንትም መካከል 318ቱ ሊቃውንት እንደ አንድ ልብ መክረ ፤ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሁነው በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት ባአንድ ቃል ሃይማኖታቸውን በመግለጥ «ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ» እስከሚለው ድረስ ጸሎተ ሃይማኖትን ደረሱ ።

318ቱ ሊቃውንት አርዮስን ከአወገዙ በኋላ ቅዱስ ጳውሎስ «ወኵሉ ዘተጽሕፈ በመንፈስ እግዚአብሔር ተጽሕፈ የተጻፈው ሁሉ በእግዚአብሔር መንፈስ ተጻፈ» ባለው ምስክርነት መንፈስ እግዚአብሔር ገልጸላቸው ፳ መጻሕፍት ደርሰው ጽፈዋል ፤ እንዚህም

ተከታዩን በ፫ኛው ገጽ ይመልከቱ ።

## መንፈሳዊ ቅስቃሴ በአዲስ አበባችን ።

ከመልአከ ሰላም ሳሙኤል ተረፈ

ከጥቂት ዓመታት አስቀድሞ በአዲስ አበባ ከተማ ከፍ ያለ መንፈሳዊ ቅስቃሴ ተፈጥሯል ።

ይህ መንፈሳዊ ቅስቃሴ በመጀመሪያ የተነሣው በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ተማሪዎች ሲሆን የተጀመረውም ትምህርት ቤቱ ሥራውን ከጀመረበት ከ፲፱፻፴፯ ዓ ም ጀምሮ ነው ። በዚህ ጊዜ የነበሩት ግብጻዊው መምህር ሰዐድ የእሑድ ትምህርት ቅስቃሴን ሲመሠርቱ፣ የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር የነበሩት ቄስ ሀብቱ ዳውድ ደግሞ ከተማሮቹ መካከል ችሎታ ያላቸውን እየመረጡ ፤ ደመወዝ እየከፈሉ ፤ በየትምህርት ቤቱ፣ በየእሥር ቤቱና በየሆስፒታሉ መላክ ጀመሩ ። በ፲፱፻፵ ዓ ም ግን ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጋር በመስማማት በክረምት ወራት ወደ የጠቅላይ ግዛቱ ሂደው እንዲሠሩ ልዩ ልብስ ፤ የኪስ ገንዘብና የዕለት ምግባቸው ታስቦ ተሰጥቷቸው በሐዋርያነት ሠርተዋል ። በዚህ ጊዜ ወደስብከት እየሄዱ የሚሠሩት መምህራን አስቀድሞ መዘጋጀት ስለነበረባቸው በመጀመሪያ በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን፣ በኋላ ግን በትምህርት ቤቱ የጸሎት አዳራሽ ስብከት ተጀመረ ።

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የተቋቋመው ይህ የተማሪዎች ማኅበር ፩ኛ ጥሩ ጥሩ ተናጋሪዎች በማፍራት ፤ ፪ኛ ለምእመናን ጥሩ ምክር በመስጠት ፤ በራዲዮም በመናገር ከፍ ያለ አገልግሎት አቅርቧል ።

ተከታዩን በ፪ኛው ገጽ ይመልከቱ ።

## ትጸልያለች

መስከረም ፲፰ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. የኢትዮጵያ ብርሃን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የወዳጅ አገሮችን ለመጐብኘት ወደ አሜሪካ አገር መሄዳቸውን ምክንያት በማድረግ ቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን ልዑል እግዚአብሔር በክንፈ ረድኤቱ ጠብቆ እንዲመልስላት እጆችዋን ዘርግታ ቀን ከሌት ጸሎት ታቀርባለች ቸርነቱ የበዛ አምላክ ተወዳጅ ንጉሠ ነገሥታችን የሄዱበትን ዓላማ አከናውነው ወዳጅ አትርፈውልን በሰላምና በጤና ወደ ውዲቱ አገራቸው እንዲመልስልን ሁላችን በግልም ሆነ በማኅበር የልቡና ጸሎት እናቅርብ ።

## የመላው አፍሪካ

### አብያተ ክርስቲያናት ፕሬዚዳንት

ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ የሐረር ሊቀ ጳጳስ ናይሮቢ ላይ በተደረገው የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ላይ የዚሁ ጉባኤ ፕሬዚዳንት ሆነው መመረጣቸውን የጉባኤው ዋና ጸሐፊ አስታውቀዋል ሲል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የውጭ አገሮች መገናኛ ክፍል ገልጿል ።

www.ethiopianorthodox.org

